# የ2011 የፓልቷክ ፖለቲካ ክፍሎች ግምገማ

በያሬድ አይቼህ - December 18, 2011

በ2011 ፓልቷክ ብቅ ስል ያዘወትርኳቸውን የፖለቲካ ክፍሎች ግምገማዎቼን ይዤላችሁ ስቀርብ በታላቅ ደስታ ነው። ግምገማው የኔ እይታ ነው ፤ መቀበልም መስማማትም የለባችሁም ፥ ግን አንብቡኝ። አላማዬ በፓልቷክ የመወያያ መድረኮች የሚደረጉትን ገንቢ የውይይት ተሞክሮዎች ለመጠቆምና ለማበረታታት ፥ በተጨማሪም ሊሻሻሉ ይገባል ብዬ ማስባቸውን የፓልቷክ የውይይት ገጽታዎች ላይ ገንቢ ትችት ለማቅረብ ነው።

የፓልቷክ ክፍሎች መከወን የሚፈልጉት አላማ ያላቸው አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ ፥ ሆኖም ግን የአላማቸው ግልጽነት አጠያያቂና አሻሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ብዙዎቹ ገና እንደተወለደ ህጻን የመንፈራገጥና የመወራጨት ባህሪ ያላቸውና ራሳቸውን በውሉ ያልቀረጹ (define) ፥ ወዴት እንደሚሄዱ ፡ ምን መሆን እንደሚፈልጉ የማያውቁ ይመስለኛል። "እየታገልን ነው" የሚል እምነት ያላቸው ወገኖችም ጥቂት አይደሉም ፥ ማንን እንደሚታገሉ ፡ እንዴት የትግላቸውን ውጤት እንደሚሰፍሩና እንደሚለኩ ግን ግልጽ አይደለም። በተጨማሪ የፓልቷክን ምንነት የሚዘነጉም አሉ። ሆኖም ግን ፓልቷክ አለ። ክፍሎቹም አሉ። ስለዚህ "ለምንድን ነው ክፍሎቹ ያሉት?" ብዬ መጠየቁ ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

## የፓልቷክ ክፍሎች ዋና አገልግሎት፡- የስሜት-ወጌሻነት (therapy)

አንድ በተደጋጋሚ በሁሉም ክፍሎች የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር ሁሉም የስሜት-ወጌሻነት (therapy) አግልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው ነው። የስሜት-ወጌሻ ማለቴ የሰዎችን ስሜት ማስተንፈሻ ፡ ማስታገሻ ፡ ማገገሚያ እና ማዝናኛ ማለቴ ነው። የፓልቷክ ክፍሎች የስሜት-ወጌሻ አገልግሎት በማወቅም ባለማወቅም እየሰጡ ነው። ለዚያ ምስጋና ይገባቸዋል። በዳያስፓራ ኑሮ የባይተዋርነት ስሜት ውጣቸውን ላጠነዘለው ወገኖቻችን ፓልቷክ የስሜት ማስተንፈሻ ስፍራ ነው። በተለይ ስደተኝነትን እንደ እርግማን ለሚያዩ ፡ አርባም አመት ይሁን አርባ ቀን በዲያስፓራ ለኖሩ ኢትዮጵያውያን ፡ ፓልቷክ መጥተው የስሜት-ወጌሻ አገልግሎት ማግኘታቸው ፥ አብያተ-ክርስትያናት ፡ መስጊዶችና ሲቪክ ድርጅቶች በሰፊው ማድረግ ያልቻሉትን ስራ የፓልቷክ ክፍሎች በሰፊው እየሰሩት ስለሆነ "ጎሽ!" የሚያስብል ነው! ምንአልባትም ፓልቷክ የስሜት-ወጌሻ አግልግሎት ማግኛ ቦታ ስለሆነ ይሆናል ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙበት ፤ ሌሎቹ አገልግሎቶቹ ግን አመርቂ ሆነው አላገኘኋቸውም።

## የፓልቷክ ክፍሎች ሌላ አገልግሎት፡- የህይወት-ቅመም

ከስሜት-ወጌሻነት በላይ ራሳቸውን የትግል ጦር ሜዳ አድረገው የሚያዩ የፓለቲካ ክፍሎች ብዙ ናቸው። ታዳሚዎችን በማሰርም ሆነ ከክፍል በማግለል የኢትዮጵያን የፓለቲካ ምህዳር ያዳበሩት የሚመስላቸው ተላላ የክፍል አስተዳዳሪዎችም አሉ። እዚህ ላይ ራሴን በተደጋጋሚ የጠየኩት "እነዚህ የፓልቷክ ታጋዮች ለምን የሚያረጉትን ያረጋሉ?" የሚል ነው። ለዚህ አንድ መልስ ሊሆን የሚችለው በስደተኝነት አለም ውስጥ የብዙ ኢትዮጵያውያን ህይወት በጣም አድካሚና አታካች ስለሆነና ፤ ከዚህ አታካችና ውጥረት የተሞላበት ኑሮ የተነሳ

ሰዎች ለህይወታቸው ቅመም ይፈልጋሉ ፤ ህይወታቸውን ትርጉም የሚሰጠውና የሚያጣፍጠው ነገር ለማግኘት ይጠማሉ ፥ ይጓጓሉ። በፓልቲክ የታጋይነት ስሜት የሚሰማቸው ወገኖቻችን ውስጣዊ ግፊታቸው የህይወት-ቅመም ፍለጋ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ህይወት ሲወጥረንና ሲያታክተን ከራሳችን በላይ የሆነ ትልቅ ጉዳይ ውስጥ እንድንገባ እና ራሳችንን ለትልቅ አላማ እንድንሰጥ እንገፋለን። የፓልቲክ ታጋይነትን ስሜት በዚህ መልክ ነው የተረዳሁት ፤ ምክንያቱም ፓልቲክን ከመረጃ ማሰራጨት ፡ ከገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብና ፡ ሃሳብን ከማንሸራሸር ያለፈ 'ትግል' ማደረግ የሚቻልበት ቦታ አይደለም።

## ጥቂቶች

ምንም እንኳን ብዙዎቹ ክፍሎች የስሜት-ወጌሻና የህይወት-ቅመም የሚሰጡ ቢሆንም ፡ ሁሉም ክፍሎች የፓለቲካ አጀንዳቸውንና ጥቅማቸውን (interest) ማስከበር እንደሚፈልጉ በየቀኑ ያውጃሉ። በየጊዜውም ተስፋ በመቁረጥ "የተረገመች አገር" የሚለውን ሙሾና ሟርታቸውን የሚደጋግሙም የተለመዱ አልቃሾችም አሉ። ሆኖም ግን ተሰሚነት ካለማግኘት ፡ ቢጤን ከማጣት ፡ ካለመመጣጠን የተነሳ መሰረታዊ ፡ አንገብጋቢና ተግባራዊ የፓለቲካ አጀንዳዎቻቸውን ለማስያዝ በተደጋጋሚ ሲማጸኑ የሚደመጡ ፡ ምራቃቸውን የዋጡ ጥቂት ወገኖች ግን አሉ። ለነዚህ ወገኖች በእርግጥ አዝንላቸዋለሁ ፥ ከማዘንም በላይ አንዳንዴ ያበሳጩኛል። እንኳን ሰዎች በማይተዋወቁበት በፓልቲክ አለም ቀርቶ ፡ ፊት ለፊትም ተዋውቀን አብረን ከመብላት እና ገንዘብ አዋጥቶ ሬሳ ከመላክ ያለፈ ፡ ዘለቄታዊ አላማ ላይ ተስማምቶ በጋራ ለመስራት መሰረታዊ ጉድለት እና ውድቀት ያለበት ማህበረሰብ መሆናችንን እንዴት ይዘነጉታል?!

# ግምገማዬ

*(ማሳሰቢያ፡- ግምገማው የግል እይታዬ ነው ፤ መቀበልም መስማማትም የለብዎትም። ግን ያንብቡኝ።)*

የማዘወትራቸውና ወጣገባ ምልባቸው የፖለቲካ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. Ethiopian Current Affairs Discussion Forum (Owner's nickname: Shibere_Desalegn)

ለ. Qale Ethiopian Vission Discussion Forum (Owner's nickname: Birtukan Midekisa)
*(ማሳሰቢያ፡- ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የክፍሉ ባለቤት **አይደሉም**። ክፍሉን የከፈተው ግለሰብ ለራሱ የሰጠው የፓልቷክ ስም (nick name) "Birtukan Midekisa" የሚል ነው።)*

ሐ. Ethio Kinjit in Switzerland (Owner's nickname: andnett)

መ. Ethiopians Forum For Political Civility (Owner's nickname: aba mela 3)

ሠ. Ethiocurrent event Assimba (Owner's nickname: Aschalew)

እነዚህን ክፍሎች ጎራ እያልኩኝ በጐበኘሁኝ ቁጥር የታዘብኳቸውን ነጥቦች ቀጥሎ አቀርባለሁ። የነጥቦቼ አላማ ከላይ እንደገለጽኩት ለመገንባት እንጂ ለማፍረስ አይደለምና በበጎ ህሊና ያንብቡኝ።

## ሀ. Ethiopian Current Affairs Discussion Forum (Owner's nickname: Shibere_Desalegn)

| የክፍሉ ጠንካራ ገጽታዎች | ሊሻሻሉ የሚገቡ ገጽታዎች |
|---|---|
| • 24/7 የተከፈተ (ሁልጊዜ ክፍት ቤት) | • ድንጉጥና ችኩል አስተዳዳሪዎች |
| • ብዛት/ቁጥር | • ያልበሰለ የፓለቲካ ግንዛቤና ስልት |
| • ሳምንታዊ ቃለምልልሶች | • የአውራዎች ብዛትና የቡድን (collective) አመራር |
| • የገንዘብ መዋጮ | • የመንጋና ጅምላ አስተሳሰብ የበላይነት |
| • ሰፊ ትውውቅ (ኔትወርክ) | • የብሄር ጥላቻና የበቀል ስሜት መንጸባረቅ |
| • ጽኑ የተቃውሞ ገጽታ | • የመቻቻል ባህል አለመኖር |
| | • አግላይነት (የኢህአዴግ ደጋፊዎችን በሙሉ ያግዳል) |
| | • ግርግርና ፡ ሁከት የበዛበት የቃለምልልስ መስተንግዶ |
| | • የጊዜ ገደብ የሌለውና የተንዛዛ የቃለምልልስ |

Current Affairs ከስሜት ወጌሻነትና ከህይወት-ቅመምነት በተጨማሪ ዘለቄታዊና ውጤታማ የሆነ የፓለቲካ ኋይል ለመሆን የሚያስችለው አመራሩ ሲዳብርና ሲበስል ብቻ ነው ብዬ አምናለሁ። ያለዚያ የእድር አመራር አስተሳሰብ ያላቸው ወገኖች ክፍሉን ሁልጊዜ መሬት ላይ ሲያስኮበኩብ እንዲኖር ነው የሚያደርጉት። አመራር ወሳኝ ነው። ብዛትና ግርግር ብቻውን እዚህ ግባ ሚባል ዘለቄታዊ ለውጥ ማምጣት የሚችል ስራ

ለመስራት በቂ አይደሉም። ከጥቂት አመታት በፊት ከክፍሉ ዋና ታዳሚዎች በከፊሉ ክፍሉን ለቀው ሌላ ክፍል እንደከፈቱ ሁሉ ፡ አሁንም ይህ ክፍል ድርጅታዊ ተሞክሮና ዘመናዊ የአመራርና የአስተዳደር ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች እንደ አማካሪ ወይንንም እንደ ቋሚ የቦርድ አባል አድርጎ ካላቀፈ የክፍሉ ህልውና ሁልጊዜ ለአደጋ የተጋለጠ ነው ብዬ እሰጋለሁ።

ክፍሉ የአመለካከት ጠባብነት በጣም ያጠቃዋል። የሰዎችን አንደበት ብቻ ሳይሆን የሰዎችን አይምሮ መቆጣጠር የሚፈልጉ አስተዳዳሪዎችና ታዳሚዎችን በተለያዩ ጊዜያት ታዝቤያለሁ። አዲስ ተናጋሪዎችን በግድ "ሞት ለወያኔ በል/በይ!" ብለው ትዕዛዝ ሚሰጡ ፋሽሰቶችም አሉበት። ክፍሉ የደርግ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያውያን ላይ ካደረሰው ጭቆናና እንግልት ምንም ያልተማሩ አውሬዎች እንዳሉበት አምናለሁ። በተጨማሪም በብሄር ላይ ያነጣጠረ የጅምላ ፍረጃ ለዚህ ክፍል ገጽታ ትልቅ መርዝ ነው። ግን ምን አልባት ይህን ክፍል ብዙዎች ሚያዘወትሩበት ምክንያንት ከጥላቻው ፡ ከጠባብነቱና ከግርድፍነቱ የተነሳ ይሆናል። ምክንያቱም ግርግርና ሁከት ፡ አምባጓሮና ጭቅጭቅ በፓልቷክ የአንድን ክፍል ታዳሚዎች ቁጥር በፍጥነት እንዲጨምር ያደርጋሉ። Current Affairsም የዚህ ክስተት ተጠቃሚ ይመስለኛል።

## ለ. Qale Ethiopian Vission Discussion Forum (Owner's nickname: Birtukan Midekisa)

*(ማሳሰቢያ፡- ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የክፍሉ ባለቤት **አይደሉም**። ክፍሉን የከፈተው ግለሰብ ለራሱ የሰጠው የፓልቷክ ስም (nick name) "Birtukan Midekisa" የሚል ነው።)*

| **የክፍሉ ጠንካራ ገጽታዎች** | **ሊሻሻሉ የሚገቡ ገጽታዎች** |
|---|---|
| • 24/7 የተከፈተ (ሁልጊዜ ክፍት ቤት)<br>• በአንጻሩ መስመር የያዩ ውይይቶች<br>• ረጋና ሰከን ያለ ገጽታ<br>• በሰፊው ሚያስቡ አንዳንድ ተሳታፊዎች<br>• ምሁራዊ (academic) ትንተናዎች ይንጸባረቃሉ | • ድንጉጥና ችኩል አስተዳዳሪዎች<br>• ያልበሰሉ መርሆች ("የግለሰቦችን ስም አናንሳ" ወዘተ)<br>• ቅጡን ያጣ አገራዊነትና እንጭጭ የፓለቲካ ግንዛቤ<br>• አግላይነት (የኢህአዴግን ፡ አነግን ደጋፊዎች አለማሳተፍ)<br>• ውይይቶች በራሳቸው ሳያልቁ አስቀድሞ ማፈን<br>• በመጠኑ ግርግር የበዛበት የቃለምልልስ መስተንግዶ |

Qale ጥሩ የስሜት ወጌሻነትና የህይወት-ቅመምነት አገልግሎት ይሰጣል። ውይይቶቹ በአንጻሩ ሰከን ያሉ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ክፍሉ ከ Current Affairs ራሳቸውን ያገለሉ ሰዎች የከፈቱት ክፍል ስለሆነ ፡ እዛኛው ክፍል ከገጠማቸው ጎጂ ተሞክሮ የተማሩ ሰዎች አሉበት። ሆኖም ግን በጣም ሰዎችን የሚያንገላታ አንድ የክፍሉ አስተዳዳሪ (Machew_2007) አለ። ያንን ወንድም ካልመከሩትና ካልገሩት ክፍሉን አደጋ ላይ ሊጥለው ይችላል።

በተለይ ስሜቱን መቆጣጠር ካለመቻሉ የተነሳና ግለሰቦችን በጣም ስለሚያንገላታ ፡ ስለሚያመናጭቅና ስለሚያዋክብ ፥ መሳተፍ ሚፈልጉ ሰዎችን ባህሪው አይስብም።

ይህ ክፍል ከ Current Affairs መልቀቁ (February 2010) ምን አይነት ለውጥ በፓልቷክ አምጥቷል ብዬ ራሴን ስጠይቅ ፥ የዚህ ክፍል መከፈት በፓልቷል ሰላማዊ ትግል የሚደግፉ ሰዎች ድምጻቸውን እንዲያሰሙ እድል ሰጥቷል። ነገር ግን በአንዳንድ ነገሮች ላይ ከCurrent Affairs ጋር ተመሳሳይነት አለው። በተለይ የገዢውን ፓርቲና የተገንጣይ ድርጅት ደጋፊዎችን Qale አያስተናግድም። ለመሆኑ በፓልቷክ ሰዎችን በማግለል ምን ለማግኘት ነው? ምንም እንኳ አንዳንድ የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች እንደ ድንጋይ የደረቁ ቢሆኑም ፤ የማይስማሙትን አመለካከት ማስተናገድ የውይይት ባህልን ያዳብራል እንጂ አያቀጭጭም። (ኢህአዴግን ፡ ኦነግንና ኦብነግን ተቃዋሚ ነኝ።)

## ሐ. Ethio Kinjit in Switzerland (Owner's nickname: andnett)

| **የክፍሉ ጠንካራ ገጽታዎች** | **ሊሻሻሉ የሚገቡ ገጽታዎች** |
|---|---|
| • ወቅታዊ ቃለምልልስ | • ግልጽ መስመር የሌለው ውይይት |
| • ጥቂት አስተዳዳሪዎች | • የኢህአዴግን አቅርቦ ፡ ኦነግና ኦብነግን መግፋት |
| • ረጋ ያለ ገጽታ | • በቅርቡ የተጀመረ የተቃዋሚ-ተቃዋሚነት ገጽታ |
| • አንጻራዊ የመቻቻል ገጽታ | • ቅጡን ያጣ ለዘብተኝነትና የፓለቲካ ሞኝነት |
| • መልክ የያዘ የቃለምልልስ መስተንግዶ | • እጅግ በጣም የተንዛዛ እንግዳ አቀባበልና አሸኛኘት |

Kinijit Switzerland ክፍል መቻቻልን በተግባር የሚያሳይ የተቃዋሚ ክፍል ነው። እንዲሁም ክፍሉ ግሩም የስሜት ወጌሻነትና የህይወት-ቅመምነት አገልግሎት ይሰጣል። ክፍሉ በአንድ ጊዜ እዚህ ደረጃ ላይ አልደረሰም። ቀስ በቀስ የመቻቻል ልምዱን ያዳበረ ክፍል ነው ፤ በጊዜ ውስጥ ያደገ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችና የኢህአዴግ ደጋፊዎች ጎን ለጎን ሲወያዩ ሳደምጥ በጣም ደስ ይለኛል ፤ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ አይነት ባህል ነው ሊዳብር ሚገባው። ነገር ግን ክፍሉ በዚህ አመት ግራ የሚያጋባና አሻሚ የሆነ ገጽታ ተላብሷል። በተለይ የክፍሉ አስተዳዳሪዎች በገዢው ፓርቲ ላይ የሚያሳዩት ቀዝቃዛነትና ለዘብተኝነት ግራ የሚያጋባ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለምን እንዲህ ሆነ?

ይህ ክፍል ከፍተኛ ወከባ እና ጥቃት ከተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ክፍሎች ደርሶበታል። አስተዳዳሪዎች ብዙ መገፋት ፡ መወረፍና ስብዕናቸውን የሚነካ ትንኮሳም ደርሶባቸዋል። በኔ ግምት የክፍሉ አስተዳዳሪዎች ከኢህአዴግ ደጋፊዎች የሚያገኙት የሞራል ድጋፍ ከደረሰባቸው ጥቃትና እንግልት እንዲያገግሙ ረድቶዋቸዋል። በተጨማሪም ከክፍሉ አስተዳዳሪ አንዱ የሆነው ወንድም (LAUREATE Tsegaye) ኢህአዴግ የሚያደረጋቸውን አንዳንድ አገራዊነትን የሚያንጸባርቁ ጉዳዮች (የአባይ ግድብ … ወዘተ) በቀላሉ ስለሚያማልሉት በፓለቲካ ጨዋታው ውስጥ የአቶ ልደቱ አያሌውን አይነት ዕጣፈንታ እየገጠመው ይመስለኛል። ኢህአዴግ ከፈለገ "ኢትዮጵያ ትቅደም!" ከማለት ወደኋላ የማይል ሙልጭልጭ ፓርቲ ነው። በፓለቲካ ውስጥ ትኩረትና ጽናት ከሌለ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ተቃዋሚው አጥቅቶናል ብሎ ወደ ኢህአዴግ ደጋፊዎች ጉያ ውስጥ መሸጎጥ ለጥቂት

ተቃዋሚ ነን ባዮች ጋጠወጦች መሸነፍ ስለሚሆን የዚህ ክፍል አስተዳዳሪዎች ተቃዋሚነታቸውን እንደቀድሞው ግልጽ ያድረጉት። ወይንም የመንግስት ደጋፊ ከሆኑም ነን ይበሉ ፥ ያም መብታቸው ነው። ግን ግራ አታጋቡኝ!

በተጨማሪም ክፍሉ በአነግና በኦብነግ ደጋፊዎች ላይ የሚያደርገው እንግልትና እቀባ የክፍሉ ትልቅ ድካም ነው። አነግና ኦብነግ የሚታገሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ ህዝቦች ነውና ማግለሉን ትቶ በውይይት በመጥመድ አቋማቸውን ለማስለወጥ መትጋት ተገቢና የበሰለ አማራጭ ነው። (አነግንም ኦብነግንም ተቃዋሚ ነኝ።)

## መ. Ethiopians Forum For Political Civility (Owner's nickname: aba mela 3)

| የክፍሉ ጠንካራ ገጽታዎች | ሊሻሻሉ የሚገቡ ገጽታዎች |
|---|---|
| • የመንግስት ተወካዮች ጋር ቃለምልልስ<br>• ሰፊ የመቻቻል ገጽታ<br>• ግሩም የቃለምልልስ መስተንግዶ<br>• ትኩረት ያለው 'የትግል' ስልት<br>• በአንጻሩ ብልህ የሆነ የፖለቲካ ግንዛቤ<br>• ታማኝነት/ሎሌነት (ለገዢው ፓርቲ) | • ጭፍንና የአድማጭን አስተሳሰብ የሚንቅ ፕሮፓጋንዳ<br>• በጣም ረዥምና አሰልቺ ንግግር (በaba mela 3)<br>• ልኩን ያለፈ አደርባይነት<br>• ጭፍን ደጋፊነት<br>• የቀድሞ የክፍሉ አባላት ላይ የማስፈራራት ዛቻዎች |

Civility ከማናቸውም ክፍሎች ይልቅ የመቻቻል ገጽታ ያንጸባርቃል። አንዴ አልፎ አዲስ አስተዳዳሪዎች ከሚያደርጉት ችኩልና ድንጉጥ እርምጃዎች ውጪ የክፍሉ አስተዳዳሪዎች ከተቃዋሚ ክፍል አስተዳዳሪዎች ጋር ሲወዳደሩ ታጋሾችና ቻዮች ናቸው። ክፍሉ በአንጻሩ ከሌሎች ክፍሎች በተሻለ የተቀናበረና የተዋቀረ ጭምር

ይመስላል። ክፍሉ ለገዢው ፓርቲ የሚሰጠው የመረጃ አቀባይነት አገልግሎት (አቃጣሪነት) ምናልባት በአንዳንድ የዳያስፓራ ተቃዋሚዎች ላይ ለፍርድ ቤት እንደ መረጃ የቀረበ ይሆን? ቢሆን አይገርመኝም።

ሌላው ጉዳይ የክፍሉ ድረገፅ (www.ethio-civility.com) በግልጽ እንደሚያመለክተው ክፍሉ የሼክ መሀመድ አልአሙዲ አገልጋይ ፡ ቅጥረኛ ወይም ሎሌ ለመሆኑ በመግቢያው ገፅ ላይ የተቀመጠው የሼሁ ፎቶና የህይወት ታሪክ ግልፅ መረጃ ነው። ሰው ከመሬት ተነስቶ የሼሁን ፎቶ ገጭ ያረጋል እንዴ? ሆ ሆ! አያረግም! አይጋፎረም (Aigaforum) እንኳ የአቶ መለስን ፎቶ በቋሚነት አለጠፈም። ይህን ስል ሼሁን ማገልገልም ሆነ መደገፍ በራሱ ችግር ነው ማለቴ አይደለም ፥ ያ የምርጫ ጉዳይ ነው። ሼሁም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የሚጫወቱት አዎንታዊ ሚና መኖሩ ግልጽ ነው። ነገር ግን የክፍሉ አስተዳደር ከአደርባይነት ነጻ አይደለም። አደርባይ የመንግስት ደጋፊዎች ፡ እንኳንስ አገራዊ ጥቅምን ሊያስቀድሙ ፡ ለሚያገለግሉትም መንግስት ዘለቄታዊ ፋይዳ የላቸውም። ጊዜውንና ወቅቱን እያዩ ከሚነፍሰው ጋር የሚነፍሱ ስለሆኑ አደገኛ ሰዎች ናቸው።

### ሠ. Ethiocurrent event Assimba (Owner's nickname: Aschalew)

| **የክፍሉ ጠንካራ ገጽታዎች** | **ሊሻሻሉ የሚገቡ ገጽታዎች** |
|---|---|
| • የኢህአፓን ትሩፋት ማውሳት | • እርስ በርስ መናከስ ('ኢህአፓ እና ኢህአፓ-ዴ') |
| • ጽኑና የማያሻማ የኢህአዴግ ተቃዋሚ | • መስዋዕትነት ያደናቀፋቸውና ያሳወራቸው አቋሞች |
| • ታሪካዊ እይታ ሚያንጸባርቁ ትንተናዎች | • የራስን ትውልድ ከአሁኑ አስበልጦ የማየት ቅዠት |
| • አለም አቀፋዊ የፖለቲካ እይታዎች | • ሰፊ የአደፍራሽነትና የእንቅፋትነት ገጽታ |
| • ተቃዋሚውን ማበጠር/ማጥራት | • የፖለቲካ ቱሪስትነትና የታሪክ እስረኛነት |

የAssimba ክፍል ዋናው ጥቅሙ የስሜት-ወጌሻነት ነው። በተለይ በተማሪው ንቅናቄ የተሳተፉ ሰዎች ከዚያ የትውልድ ትስስራቸው የተነሳ ተሰብስበው ስላለፈው የሚተርኩበት ፡ አሁን ስላለው የሚዶልቱበትና የሚያቅራሩበት ክፍል ነው። ኢህአፓ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ታሪክ ውስጥ ከማንም በላይ ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈሉ የታሪካዊ ጭብጥ ነው። ሆኖም ግን ያ መስዋዕትነት ያስገኘው ውጤት በአንጻሩ ትንሽ ነው። ያንን እውነታ የAssimba ታዳሚዎች በውሉ ስለሚያቁት ይመስለኛል ጽኑ የሆነ የተቃውሞ ብቻ ሳይሆን የጥላቻ አቋም በገዢው ፓርቲ ላይ ያላቸው። መብታቸው ነው። ሆኖም ግን በዚህ ክፍል የሚንጸባረቀው የአደፍራሽነትና የእንቅፋትነት ገጽታ መስዋዕትነት መክፈል ምን ያህል አስከፊ የሆነ የአስተሳሰብ አዙሪኝ ውስጥ እንደሚጥል ግልጽ ነው። ኢህአዴግም የዚሁ አዙሪት ክፉኛ ሰለባ ነው። መስዋዕትነት መክፈል የይገባኛል ስሜት ይፈጥራል። ኢህአፓዎች የዚህ ስሜት የእድሜ ልክ እስረኛ ሆነዋል።

ሌላው የዚህ ክፍል ገጽታ የፓለቲካ ቱሪስትነት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሚሆነውን ነገር እንደ ትዕይነትና እንደ ሲኒማ የሚያዩ ያሉ ይመስለኛል። ቱሪስቶች ተሳታፊ አይደሉም ተመልካች እንጂ። ቱሪስቶች ከውጪ ወደ ውስጥ ነው ሚያዩትና ነገሮችን ያዛንፋሉ። ኢህአፓዎችም ሁሉ ነገር በነሱ ትውልድ ያለቀ ፡ የደቀቀ ይመስል ፤ ነገሮችን ከነሱ ትውልድ ውጭ ማየት የተሳናቸው ይመሰላል። ይህ ሁሉ ግን ከመድማት ፡ ከመቁሰል ፡ ከመሰደድ የተነሳ ስለሆነ ምናልባት ፓልቲክ ለኢህአፓዎች ግሩም የስሜት-ወጌሻ ሆኖዋቸዋል።

ጽ ጬ

ጸሃፊውን ለማግኘት፡- yared_to_the_point@yahoo.com